# የኢትዮጵያ
# የጤና ድጋፍ
# ማህበር

## ስራዎቻችን

በብሪታኒያ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የተለያዩ ጤና ነክ አገልግሎቶችን እንሰጣለን። ሥራችንን የምናከናዉነዉ የኢትዮጵያዉያንን ባህል፤ ስነልቦናና ቋንቋ ከግምት ዉስጥ በማስገባት፤ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎችና በበጎ ፈቃደኝነት በሚያገለግሉ ሰራተኞች ሲሆን የተጠቃሚዎች መረጃም በሚስጥር ይያዛል።

## ድርጅቱ የሚሰጣቸዉ ዋና ዋና አገልግሎቶች፡

- የምክር አገልግሎት መስጠት (Counselling & advice)
- በቀጠሮ ላይ በመገኘት የቃል በቃል ትርጉም መስጠት
- ሕሙማንን በቤታቸውና በሆስፒታሎች መጠየቅ
- እንደበሽተኛው ሆኖ የጤና ባለሙያዎችን ማነጋገርና ማስረዳት
- ጤና ነክ የሆኑ ጠቃሚ ጽሁፎችን መተርጎምና ማሰራጨት
- ኮንዶምና የመሳሰሉትን የአባለዘር በሽታ መከላከያዎችን በነጻ ማደል
- በሬዲዮና በቴሌቪዥን ጤና ነክ መረጃዎችን ማስተላለፍ
- ጤና ነክ ስብሰባዎችንና አውደ ጥናቶችን ማዘጋጀት
- በጤና ችግር የሚፈጠር ስራ አጥነትን ከሌሎች ድርጅቶች ጋር በመተባበር መፍትሄ እንዲያገኝ መርዳት፤
- በአጠቃላይ ኢትዮጵያዊያን ስደተኞች ከሚኖሩበት ሃገር ህብረተሰብ ጋር በመተሳሰር አብሮ መኖር እንዲችሉ ማበረታታትና ማገዝ።

## በበለጠ ለመረዳት

የድርጅቱን አስተባባሪ አቶ ክፍአለ ዓለሙን ወይም የጤና ገልገሎት ሰራተኛዉን አቶ ሀይሌ ብዙአየሁን በመደወል ወይም ጽህፈት ቤቱ ድረስ በመምጣት ያነጋግሩ።


አድራሻችን፡ Priory House<br>
Kingsgate Place<br>
London NW6 4TA

ስልክ ቁጥር፡ 020 7419 1972<br>
ፋክስ 020 7691 2385<br>
ኢሜል admin@ethsa.co.uk<br>
ድረ ገጽ www.ethsa.co.uk